የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፫
አዲስ አበባ ጥቅምት ፳፬ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም

ኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

22nd Year No. 3
ADDIS ABABA, 4th November,2015

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፶፩/፪ሺ፰

የደምቢ ዶሎ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........................ ገጽ ፰ሺ፭፻፷፬

Council of Ministers Regulation No.351/2015

Dembi Dolo University Establishment Council of Ministers Regulation ----------------------------Page 8564

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፶፩/፪ሺ፰ ዓ.ም

## የደምቢ ዶሎ ዩኒቨርስቲን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፱፻፲፮/፪ሺ፰ አንቀጽ ፭ እና ፴፱ እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፮፻፶/፪ሺ፩ አንቀጽ ፭(፩) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ "የደምቢ ዶሎ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፶፩/፪ሺ፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. <u>መቋቋም</u>

፩/ የደምቢ ዶሎ ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No.351/2015

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF DEMBI DOLO UNIVERSITY

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 and 39 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 916/2015 and Article 5(1) of the Higher Education Proclamation No. 650/2009.

1. **Short Title**

   This Regulation may be cited as the "Dembi Dolo University Establishment Council of Ministers Regulations No. 351/2015".

2. **Establishment**

   1/ Dembi Dolo University (hereinafter the "University") is hereby established as an autonomous higher education public institution having its own legal personality.

፪/ የዩኒቨርስቲው ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል።

፫/ ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፮፻፶/፪ሺ፩ እና በፌደራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፲/፪ሺ፫ መሠረት ይተዳደራል።

**፫.** **<u>ዋና ግቢ</u>**

የዩኒቨርሲቲው ዋና ግቢ በደምቢ ዶሎ ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል።

**፬.** **<u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ቀን ጥቅምት ፳፬ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

2/ The University shall be accountable to the Ministry of Education.

3/ The University shall be governed by the Higher Education Proclamation No. 650/2009 and the Federal Universities Council of Ministers Regulation No. 210/2011.

**3. <u>Main Campus</u>**

The University shall have its main campus at Dembi Dolo Town and may establish elsewhere other academic units and centers of research and community services.

**4. <u>Effective Date</u>**

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 4th day of November, 2015.**

**HAILEMARIAM DESALEGN**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**